በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገቢዎች ሚኒስቴር ሀዋሳ ቅ/ጽ ቤት
THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES
HAWASSA BRANCH OFFICE

ቁጥር Ref.No 20.10/637/46/72
ቀን Date ሐምሌ 16 2017

ለ-ሁሉም ግብር ከፋዮች

ጉዳዩ፡- <u>የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 1395/2017 አተገባበርን ይመለከታል</u>

1.በአዋጁ አንቀፅ 97 የቅድመ ግብር (withholding tax) በተመለከተ፣

1/ከጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ በስተቀር ማንኛውም ድርጅት፤ የመንግስት መስሪያ ቤት፤ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ወይንም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ግብር ቀንሰው እንዲያስቀሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ግብር ከፋዮች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ ላይ 3% (ሶስት በመቶ) ግብር ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ አለባቸው፦

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ግዢ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት የሚፈጸም ክፍያ፤

ለ) በኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ የአገልግሎት አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አስር ሺህ ብር) በላይ የሚፈጸም ክፍያ፤

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተፈጻሚ የሚሆንበት አቅራቢ ግብር ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን እና የታደሰ ንግድ ፈቃዱን ያልሰጠ እንደሆነ ግብሩን ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ያለበት ሰው ከሚፈጽመው ጠቅላላ ክፍያ ላይ 30% (ሰላሳ በመቶ) ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ አለበት፡፡

2በአዋጁ አንቀጽ 64 ያልተከፋፈለ ትርፍ (divedend) በተመለከተ፣

1/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በአንድ የግብር አመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባለቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ የተጣራ የድርጅቱ ትርፍ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ግብር ይከፈልበታል፡፡

2/ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "ያልተከፋፈለ ትርፍ" ማለት የኩባንያው የሒሳብ ዓመት ካለቀ በኋላ ባሉት አስራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ ወይም የኩባንያውን ካፒታል ለመጨመር ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው በቋሚነት በሚሰራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ስራ ለሚያካሂድ የውጭ አገር ኩባንያ ያልተላከ ትርፍን ያካትታል፡፡

3.በአዋጁ አንቀጽ 23 አማራጭ አነስተኛ ግብር በተመለከተ፣

1/በዚህ አዋጅ ወይም በሌላ ማናቸውም ህግ የተደነገገው ቢኖርም፤ ማናቸውም ድርጅት ወይም ሰው ግብር በሚወሰንበት የግብር አመት ከሁሉም የንግድ ስራ የገቢ ምንጮች ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባው ግብር በዚሁ የግብር አመት ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ከ2.5% (ከሁለት ነጥብ አምስት በመቶ) በታች ከሆነ ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከተው የማስከፈያ መጣኔ መሰረት አማራጭ አነስተኛ ግብር መክፈል አለበት

4.በአዋጁ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 1 ተራ ፊደል (ኘ) በአንድ ቀን ውስጥ በጥሬ ገንዘብ (cash transaction) የሚፈጸም ግብይትን በተመለከተ ፣

ማናቸውም ግብር ከፋይ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ ቼክ፤ ወደ ባንክ ሂሳብ ገቢ ከሚደረግ የባንክ ድራፍት፤ ከአንድ የባንክ ሂሳብ ወደሌላ የባንክ ሂሳብ እና ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው የክፍያ

ለዘመናዊና ፍትሃዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ. 0462211328 ኢሜይል :erca@ethionet.et ፖ.ሣ.ቁ: 324
Tel 0462123962 Email P.O.Box
ፋክስ 0462125297 ድረ ገጽ: WWW.erca.gov
Fax Web site Hawassa, Ethiopia
የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry Of Revenue Hawassa Branch

ቁጥር _____
Ref.No
ቀን_____
Date

መፈጸሚያ መንገዶች ገንዘብ ከማስተላለፍ ውጪ በአንድ ቀን ውስጥ ለአንድ ሰው ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) በላይ በሆነ ጥሬ ገንዘብ የፈጸመው ወይም የፈጸማቸው ክፍያዎች ተቀባይነት እንደሌላቸው ተደንግጓል።
ስለሆነም ከላይ የተዘረዘሩትንና ቀድሞ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ 979/08 ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ከታች በተገለጸውመሰረት ተግባራዊ ስለሚሆኑ የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 1395/2017 አዚህ ማሳሰቢያ ጋር አባሪ አድርገን የላክንና በተጨማሪም በተቋሙ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት የምትችሉ መሆኑን እያሳወቅን ላልተፈለገ ወጪ እና ተጠያቂነት እንዳትዳረጉ እናሳስባለን ::

ይህ አዋጅ ከሚከተለው ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፦

1) በዚህ አዋጅ የተጣለው አማራጭ አነስተኛ ግብር ከሃምሌ 1ቀን 2017 አ.ም ጀምሮ በሚሰበሰብ ግብር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤
2) በሰነጠረዥ "መ" መሰረት የሚሰበሰብ ግብር እና በተሸጋሸገው አንቀጽ 97 መሰረት ከግብይቶች ላይ ተቀናሽ የሚደረገው ግብር ከነሃሴ 1 ቀን 2017 አ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፤
3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች የዚህ የማሻሻያ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት ከሀምሌ 1 ቀን ጅምሮ በተገኘ ገቢ ላይ ይሆናል።

ለበለጠ መረጃ

- 0462211328 ኢሜል ercahawassa@gmail.com
- 0462123682 ድረ ገጽ፡ WWW.erca.gov.et
- 0462206627
- 0462123831 ቴሌግራም https://t.me/MORHawassaBranch/3326
- 0462217082

ከሰላምታ ጋር!

ፍሬህይወት አድማሱ ደጀኔ
Frehiwot Admasu Dejene
የታክስ አፕሬሽን ም/ስራ አስኪያጅ
Deputy Manager

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry Of Revenue Hawassa Branch